## ድንግል ሆይ! በኃጢአት በፍትወት የተጸነስሽ አይደለሽም!

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!

እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ "መሠረቶቿ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው" ብሎ ልበ አምላክ ዳዊት በመዝሙሩ ስለዘመረላት፤ ዳግመኛም ቅዱስ ያሬድ "ማርያምሰ ተንተ እምትካት ውስተ ከርሱ ለአዳም ከመ ባሕርይ ጸዓዳ- ማርያምስ ከጥንት ጀምሮ በአዳም ባሕርይ ውስጥ እንደ ነጭ ዕንቁ ታበራለች (በደፈረሰው ዓለም በንጽሕና በቅድስና በድንግልና ታበራለች)" ብሎ ስለተናገረላት፤ ዳግመኛም "እግዚአብሔር አብ በሰማይ ሆኖ ምሥራቅንና ምዕራብን ሰሜንና ደቡብን ዳርቻዎችን ሁሉ በእውነት ተመለከተ፤ ተነፈሰ አሸተተም፤ እንደ አንቺ ያለ አላገኘም፤ የአንቺ መዐዛ ወደደ የሚወደውን ልጁንም ወደ አንቺ ላከ" ብሎ ሊቁ አባ ሕርያቆስ ስለተቀኘላት የእመብርሃን ነገረ ጽንሰቷን እንናገራለን።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሥርወ ሃይማኖት ከሚሆን ከአብርሃም ሥርወ መንግሥትም ከሚሆን ከዳዊት ወገን እንደ ተገኘች ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የመሆን ምሥጢር በተናገረበት አንቀጽ፡- "እስመ አኮ እመላእክት ዘነሥኦ ለዘነሥኦ ዘእንበለ ዳዕሙ እምዘርአ አብርሃም- የነሣውን ባሕርይ ከአብርሃም ነሣው እንጂ ከመላእክት የነሣው አይደለም" አለ /ዕብ.2፡16/። በዚህ መሠረት ወላዲተ ቃል ቅድስት ድንግል ማርያም የአብርሃም ዘር መሆኗን አወቅን ተረዳን ማለት ነው። ልዑለ ቃል ኢሳይያስም፡- "ትወጽእ በትር እም ሥርወ እሴይ- ከእሴይ ሥር (ከእሴይ ነገድ) ብትር (እመቤታችን) ትወጣለች (ትወለዳለች)፤ ወየዓርግ ጽጌ እምኔሃ- አበባም ከግንዱ ይወጣል (ከእርሷም ጌታ ይወለዳል) " አለ /ኢሳ.11፡1፤ ንባቡና ትርጓሜው በአንድምታ/።

ሊቃውንቱ እንደሚነግሩን የእመቤታችን ነገረ ጽንሰቷ እንደሚከተለው ነው፡-
ቅድመ አያቶች የሚሆኑ ጌጥርቃና ቴክታ የሚባሉ ሰዎች በኢየሩሳሌም ተጋብተው ይኖሩ ነበር። እነዚህ ቅዱሳን ይህ ቀራቸው የማይባሉ ባለጸጎች ቢሆኑም የሚወርሳቸው ልጅ አልነበራቸውም። ከዕለታት በአንዱ ቀን ግን ጌጥርቃ ሚስቱ ቴክታን፡- "እኅቴ ቴክታ ሆይ! እኔ መካን፤ አንቺ መካን ይህ ሁሉ ገንዘብ ለማን ይሆናል?" አላት። ቴክታም መልሳ፡- "ወንድሜ ሆይ! እግዚአብሔር ለእኔ ልጅ ቢነሳኝ አንተም እንደኔው ሆነህ ትቀራለህን? ይሰጥህ ይሆናልና ከሌላ ደርሰህ ውለድ" አለችው። እርሱም፡- "ይህስ እንዳላደርገው አምላከ እስራኤል ያውቃል" አላት። በዚህ ጊዜ አዘኑ። ወዲያውም ራዕይ አዩ። ነጭ እንቦሳ

ከበረታቸው ስትወጣ እንቦሳይቱ እንቦሳ እየወለደች እስከ ስድስት ስትደርስ ስድስተኛይቱም ጨረቃ ጨረቃይቱም ፀሐይን ስትወልድ አዩ፡፡

ከዚህ በኋላ መፈክረ ሕልም (ሕልምን የሚተረጉም) ጋር ሄዱና ያዩትን ሁሉ ነገሩት፡፡ እርሱም "እግዚአብሔር በምሕረቱ ጎብኝቷችኋልና ደግ ልጅ ትወልዳላችሁ፡፡ ሰባት እንስት ጥጆች መውለዳችሁ ሰባት ሴቶች ልጆችና የልጅ ልጆች መውለዳችሁ ነው፡፡ ስድስተኛይቱ ጨረቃም ከፍጡራን በላይ የምትሆን ልጅ ነች፡፡ የፀሐይ ነገር ግን አልተገለጸልኝም፤ እንደ ነቢይ እንደ ንጉሥ ይሆናል" አላቸው፡፡ እነርሱም ጊዜ ይተርጉመው ብለውት ሄዱ፡፡

ከዚህ በኋላ ቴክታ ፀነሰች፤ ወለደችም፡፡ ስሟንም "ረከብኩ ስእለትዬ፤ ረከብኩ ተምኔትዬ-የተሳልኩትን አገኘሁ፤ የተመኘሁትን አገኘሁ" ስትል ሄኤሜን አለቻት፡፡ ሄኤሜን ዴርዴን፣ዴርዴ ቶናን፣ ቶና ሲካርን፣ ሲካር ሄርሜላን፣ ሄርሜላ ሐናን ወለደች፡፡ ቅድስት ሐናም አካለ መጠን ስትደርስ ከቤተ ይሁዳ ለተወለደ ኢያቄም ለሚባል ደግ ሰው አጋቧት፡፡

ኢያቄምና ሐና ኑሮአቸው በእግዚአብሔር ፊት ቅንና ግልጽ በሰውም ፊት የዋሃንና ስሕተት የማይታይባቸው ደጋግ ሰዎች ነበሩ፡፡

በዚህ ሁኔታ በሰውና በእግዚአብሔር የተመሰገኑ እነዚህ ደጋግ ሰዎች ልጅ ሳይኖራቸው ሃያ ዓመታት አለፉ፡፡ ተወዳጆች ሆይ! እኛ ምን ያህል ታጋሾች እንሆን? ምን ያህል እግዚአብሔርን እንጠብቅ ይሆን? ምን ያህል እግዚአብሔርን እንለማመጥ ይሆን? እነዚህ ቅዱሳን ግን ሃያ ዓመታት ጠበቁ፡፡ ዝም ብሎ መጠበቅ አይደለም፡፡ በጸሎትና በልመና እንጂ፡፡

ከዕለታት በአንዱ ቀን ኢያቄም፡- "አቤቱ ጌታዬ የአባቶቼ አምላክ ሆይ! እኔ ባርያህ እለምንሃለሁ፤ አትናቀኝ ጸሎቴን ስማኝ፤ ፈቃዴን ፈጽምልኝ፤ ለዓይኔ ማረፍያ ለልቤ ተስፋ የሚሆን የተባረከ ወንድ ልጅ ስጠኝ" ብሎ ሲለምን ዋለ፡፡ ሐናም በበኩሏ፡- "አቤቱ ጌታዬ የአባቶቼ የእስራኤል አምላክ! እኔ ባርያህ እለምንሃለሁ፤ ስማኝ ለዓይኔ ማረፍያ ለልቤም ተስፋ የምትሆን የተባረከች ሴት ልጅ የማሕጸኔን ፍሬ ስጠኝ" ስትል ዋለች፡፡

እንዲህም ብለው ሲጸልዩ ሲለምኑ ውለው ርግብ ከልጆቿ ጋር ስትጫወት አይታ ሐና፡- "አቤቱ ጌታዬ ለዚህች ግእዛን ለሌላት እስንስሳ ልጅ የሰጠህ አምላክ ምነው ለእኔ ልጅ ነሳኸኝ ብላ " ምርር ብላ አለቀሰች፡፡

ስለዚህ ኢያቄምና ሐና እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣቸው አብዝተው ለመኑ፡፡ "ወንድ ልጅ ብንወልድ ወጥቶ ወርዶ አርሶ ቆፍሮ ይርዳን አንልም፤ ለቤተ

እግዚአብሔር አንጣፊ ጋራጅ ሆኖ ይኖራል እንጂ፡፡ ሴት ልጅም ብንወልድ እንጨት ሰብራ ውኃ ቀድታ ትርዳን አንልም፤ ለቤተ እግዚአብሔር መሶበ ወርቅ ሰፍታ መጋረጃ ፈትላ ትኑር እንጂ" ብለውም ቃል ገብተው ተሳሉ፡፡

ቅድስት ሐናና ቅዱስ ኢያቄምም ዕለቱን ራዕይ አይተው ነገር አግኝተው አደሩ፡፡ ኢያቄም "ሰባቱ ሰማያት እንደ መጋረጃ ተገልጠው ከላይኛው ሰማይ ነጭ ወፍ ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥ አየሁ" አላት፡፡ ወፍ የተባለው ጌታችን ሲሆን ነጭነቱም ንጹሐ ባሕርዩን የሚያሳይ ነው፡፡ በራሴ ላይ ሲቀመጥ አየሁ ማለቱም ጌታ የኢያቄምን (የሰውን) ባሕርይ ባሕርይ አድርጎ መውረዱን ነው፡፡ ሰባቱ ሰማያት የተባሉት የጌታችን የተለያዩ ባሕርያት ሲሆኑ እነርሱም ምልአቱ፣ ስፍሐቱ፣ ርቀቱ፣ ልዕልናው፣ ዕበዩ፣ መንግሥቱ እንደዚሁም እዘዙ ናቸው፡፡

ሐናም እኔም አየሁ አለችው፡፡ ምን አየሽ ቢላት፡- "ነጭ ርግብ መጥታ በራሴ ላይ ወርዳ በጆሮዬ ገብታ በማሕፀኔ ስትተኛ አየሁ" አለችው፡፡ ርግብ የተባለች እመቤታችን ስትሆን ነጭነቷም ንጽሕናዋ፣ ቅድስናዋ ድንግልናዋ ነው፡፡ "በጆሮዬ ገብታ በማሕፀኔ ስትተኛ አየሁ" ማለቷ ደግሞ በመልአኩ ብሥራት እመቤታችንን መፅነሷን ነው፡፡ ይህም የሆነው ሐምሌ ሠላሳ ነው፡፡

እነርሱም እንዲህ ያለ ራዕይ ካየን ነገር ካገኘን ብለው ዕለቱን ሩካቤ አልፈጸሙም፡፡ አስቀድመው ፈቃደ እግዚአብሔርን ጠየቁ እንጂ፡፡ በኢየሩሳሌም በቤተ መቅደስ በዓል ሲከበር ኢያቄም ከጐረቤቶቹ ጋር መባዕ ይዞ በዓሉን ለማክበር ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ፡፡ በጊዜው የነበረው ሊቀ ካህናትም ይሳኮር (ሮቤል) ይባላል፡፡ ኢያቄም መሥዋዕት ይዞ መምጣቱን አይቶ ወደ እርሱ ሄደና፡- "ልጅ ሳይኖርህ (መኻን ስትሆን) እንዴት ወዲህ ትመጣለህ? መባንስ እንዴት ታቀርባለህ? እግዚአብሔር እኮ የመካኖች መባ አይቀበልም" አለና ከለከለው፡፡ ኢያቄምም በከፍተኛ ሐፍረትና ሐዘን ተመለሰ፡፡ ሰዎች በራችን ይዘጋሉ፤ እግዚአብሔር ግን ይከፍትልናል፡፡ ሰዎች "ምን ያደክምሃል?" ይሉናል፤ እግዚአብሔር ግን ይደግፈናል፡፡

ስለዚህ በዚህ ጊዜ ታላቅ ብርሃን የተጐናጸፈ የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ በኢያቄም ፊት ቆመ፡፡ እንዲህም አለው፡- "ኢያቄም ሆይ! እኔን በማየት አትፍራ፤ አትጨነቅም፡፡ እኔ ጸሎትህ እንደተሰማ ምጽዋትህም ቅድመ እግዚአብሔር እንደደረሰ ልነግርህ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወዳንተ የተላክሁ የእግዚአብሔር መልአክ ነኝ፡፡ ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ የብዙዎችን ማሕፀን ይዘጋል፤ ይከፍታልም፡፡ የጥንቷ እናትህ ሣራ እስከ ሰማንያ ዓመት ዕድሜዋ መካን ሁና በኋላ ግን የይስሐቅ እናት ሆነች፡፡ እንደዚሁም ራሔል የእግዚአብሔር ወዳጅ ሁና መካን ነበረች፤ በኋላ ደግሞ የዮሴፍ እናት ሆነች፡፡ የእግዚአብሔር የቅርብ ወዳጅ የነበሩት የሳምሶንና የሳሙኤል እናቶች መካን ነበሩ፤ በኋላ ግን የእነዚህ ታላላቅ

ሰዎች እናቶች ሆኑ /መሳ.13፡1-24፣ መሳ.1፡20/፡፡ ስለዚህ ሚስትህ ሐና ሴት ልጅ ትወልድልሃለች፤ ስሟንም ማርያም ብለህ ትጠራታለህ፡፡ በእናትዋ ማሕፀን ውስጥ ሳለችም መንፈስ ቅዱስ ያድርባታል"፡፡

ዳግመኛም መልአኩ ወደ ሐና ሄደና እንዲህም አላት፡- "ሐና ሆይ! ሌላ መንፈስ ያየሽ አይምሰልሽ! እኔ ጸሎትሽንና ምጽዋትሽን ከእግዚአብሔር ፊት የማቀርብ መልአክ ነኝና፡፡ አሁንም የመጣሁት ከሴቶች ሁሉ በላይ የምትሆን ስሟም ማርያም የምትባል ልጅ የምትወልጂ መሆንሽን ልነግርሽ ነው" በማለት አበሠራት፡፡ በዚህ እውነት፣ በብሥራተ መልአክ፣ በፈቃደ አምላክ እመ አምላክ እመቤታችን ከአባትዋ ከኢያቄም ከእናትዋም ከሐና ነሐሴ ሰባት ቀን በ5484 ዓመተ ኵነኔ ሲፈጸም ተጸነሰች፡፡ ግንቦት አንድ ቀን በ5485 ዓመተ ኵነኔ ሲፈጸም ተወለደች፡፡

ኦ ድንግል አኮ በፍትወተ ደነስ ዘተጸነስኪ አላ በሩካቤ ዘበሕግ እም ሐና ወኢያቄም ዘተወለድኪ፡፡ ድንግል ሆይ! በኃጢአት በፍትወት የተጸነስሽ አይደለሽም፤ በሕግ በሆነ በሩካቤ ከሐናና ከኢያቄም ተወለድሽ እንጂ፡፡

ድንግልናን ከእናትነት፣ አገልጋይነትን ከእናትነት፣ ወተትንም ከድንግልና አስተባብረሽ የያዝሽ እመቤታችን ሆይ! ከገነት በተባረርን ጊዜ ተስፋችን የተፈጸመብሽ አንቺ ነሽና እናወድስሻለን፤ ብጽዕት ሆይ እንልሻለን፤ ቅድስት ሆይ እንልሻለን፡፡ ይኸውም አንደበታችን የሚችለውን ያህል መናገራችን እንጂ ምስጋናሽንስ የኪሩቤል አንደበትም ማድረስ አይቻለውም፤ የሱራፍኤል አንደበትም ተናግሮ አይፈጽመውም፡፡ ከወዳጅሽ ከልጅሽ ምሕረትንና ይቅርታን ለምኝልን፡፡ አሜን ለይኩን ለይኩን!!!!!!!!!!


<u>ዋቢ</u>

1.ቅዳሴ ማርያም አንድምታ
2.ነጭ ዕንቁ በአዳም ገላ
3.ትንቢተ ኢሳይያስ ንባቡና ትርጓሜው
4.ስንክሳር- የዲ/ን መልአኩ እዘዘው ገጽ

ነገረ ማርያም- ክፍል ፩ (መግቢያ)

(መቅረዝ ዘተዋሕዶ፣ ታኅሳስ ፩ ቀን፣ ፳፻፮ ዓ.ም.)፡- በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!!

ይህ የነገረ ማርያም (Mariology) ትምህርት ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ከፅንሰቷ ጀምሮ እስከ ዕርገቷ ስላለው የሕይወቷን ዝክረ ታሪክ፣ ስለ እመ አምላክነቷ፣ ስለ ዘላለማዊ ድንግልናዋ፣ በነገረ ሥጋዌ ስላላት ሱታፌ (ድርሻ)፣ ስለ ንጽሕናዋና ስለ ተሰጣት ክብር የምናጠናበት የሃይማኖት ትምህርት ክፍል ነው፡፡



የክርስትና እምነት በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምላካዊ የቤዛነት ሥራ፣ በፈሰሰው ወርቀ ደም የተመሠረተ የሕይወትና የድኅነት መንገድ ነው፡፡ ስለዚህም በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት ነገረ ድኅነት (Soteriology) የትምህርተ ሃይማኖት ሁሉ አክሊል (ጉልላት) ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚነግሩን በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድና ሥምረት በጥንተ ተፈጥሮ የተፈጠረው የሰው ልጅ ዳግመኛ በሐዲስ ተፈጥሮ በመታደሱ ምክንያት በመንፈስ ልደት ከብሯል፡፡ "ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው አልፎአል፤ ሁሉም እንሆ አዲስ ሆኗል" /2ቆሮ.5፡17/፤ "አባ አባት ብለን የምጮህበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ"

/ሮሜ.8፡15/፤ “ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑ ለእነርሱ ደግሞ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው” /ዮሐ.1፡12/፤ “ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፤ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ” /2ጴጥ.1፡23/ የሚሉት ቃላተ መጻሕፍት ይህን እውነት የሚያስረዱ ናቸው፡፡

ይህ አምላካዊ የቸርነት ሥራም አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በተዋሕዶ በነሣው ሥጋና ነፍስ የተከናወነ ነው፡፡ ስለሆነም የዚህ ፍሬ ድኅነት ተካፋዮች የሆንን ክርስቲያኖች ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስን ስለወለደች፣ የሰው ልጅ የመዳን ቀን ከሰው ልጆች በቅድሚያ ስላወቀች፣ ለእግዚአብሔር የማዳን ሥራ መሣርያ በመሆን አዳኙን መሲሑን ስለወለደች፣ የእግዚአብሔር ታማኝ የምሥጢር መዝገብ ስለሆነች ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ከፅንሰቷ ጀምሮ እስከ ዕርገቷ ስላለው የሕይወቷን ታሪክ፣ ስለ እመ አምላክነቷ፣ በነገረ ድኅነት ውስጥ ስላላት ወሳኝ ሚናና ከፍተኛ ሱታፌ፣ ስለ ዘላለማዊ ድንግልናዋ፣ ስለ ንጽሕናዋና ስለ ተሰጣት ክብር በሚገባ ጠንቅቀን ማወቅና መረዳት ይገባናል፡፡

ወደ ኋላ መለስ ብለን የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ስንመረምር ስናጠና ከአንደኛው እስከ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ነገረ ክርስቶስን (Christology) ከነገረ ማርያም (Mariology) ጋር ያለውን ጥልቅ የምሥጢር ግንኙነት በመረዳታቸው ምሥጢረ ሥጋዌን ከማስተማራቸው አስቀድሞ ነገረ ማርያምን በጥልቀት ይማሩና ያስተምሩ እንደ ነበር እናስተውላለን፡፡ ይህ ጥልቅና ድንቅ ምሥጢር ስፍሐ አእምሮ ያላቸውና የነገረ መለኰትን ትምህርት (Theology) በቅጥነተ ኅሊና የመመርመርና የማራቀቅ ተውህቦና ክኅሎት የተሰጣቸው እነዚህ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ባስተማሩት ሕያው ትምህርትና በጻፏቸው አያሌ የአዕማደ ምሥጢር (Pillars Of Mystery) መጽሐፎቻቸው ከርሠ ምሥጢር እንደ ዕንቁ ፈርጥ ሲያበራ የምናገኘው ነው፡፡ ሊቃውንቱ በትምህርታቸው ሁሉ ነገረ ማርያም የሃይማኖት ክፍል (Dogma) መሆኑን አብራርተው ገልጠውታል፡፡ ምክንያቱም “ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት የተወለደው ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አካላዊ ቃል 5500 ዘመን ሲፈጸም ያለ አባት ከቅድስት ድንግል ማርያም በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ በኅቱም ድንግልና ተወለደ፤ እርሱ በእውነት የባሕርይ አምላክ ነው፤ እርሷም በእውነት የአምላክ እናት ናት” ብሎ መመስከር ሃይማኖት ነውና፡፡ ማንኛውም በድንግል ማርያም ላይ የምንናገረው ነገር ነገረ ክርስቶስንና ነገረ ድኅነትን የሚነካ በመሆኑ ሃይማኖት ነው፡፡

ጥንታዊት፣ ሐዋርያዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲያናችንም ይህን ይዛ በዘወትር ሥርዓተ አምልኮቷ ጊዜ በምትገለገልባቸው የተለያዩ የጸሎትና የቅዳሴያት መጻሕፍት ሁሉ የነገረ ማርያም አስተምህሮዋን በስፋትና በጥልቀት ትመሰክራለች፡፡ ይልቁንም ደግሞ ፍጹም ሰማያዊና መንፈሳዊ የሆነው ሥርዓተ

ቅዳሴዋ በማኅፀነ ድንግል ማርያም የተጀመረውን፣ በድንግልናዊ ልደት የተገለጠውን፣ በቀራንዮ አደባባይ የተፈጸመውንና በዕለተ ትንሣኤ የተረጋገጠውን የድኅነተ ዓለም ጉዞ ዘወትር የሚያዘክርና የነገረ ማርያምና የነገረ ድኅነት የምሥጢር መድብል ነው፡፡ በዚህም የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ሁለንተናዊ ሕይወት ከእግዚአብሔር የማዳን ሥራ (Soteriology) ጋር በእጅጉ የተዋሐደና በቀጥታ የተገናኘ መሆኑን እናስተውላለን፡፡

ክብሯ ከመላእክትና ከደቂቀ አዳም ሁሉ ከፍ ከፍ ያለ መሆኑ፤ የባሕርይ አምላክ አካላዊ ቃል ክርስቶስን በኅቱም ድንግልና ፀንሳ በኅቱም ድንግልና የወለደች በመሆኗ ወላዲተ አምላክ (Theotokos- Mother Of God)፣ እመ እግዚአብሔር ጸባኦት፣ እመ ብርሃን፣ ማኅደረ መለኮት እያለች ሥያሜዋን ታስተምራለች፡፡ በሥጋዋ በኅሊናዋ ድንግል በክልኤ የተባለች ቅድስት ድንግል ማርያም ቅድመ ፀኒስ ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ፀኒስ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ፀኒስ ድኅረ ወሊድ ጽንዕት (Perpetual Virgin) ናት፡፡ በመሆኑም አምላክን ስትወልደው ማኅተመ ድንግልናዋ አለመለወጡ አምላክም ሰው ሲሆን ባሕርየ መለኮቱ ላለመለወጡ፣ ዳግመኛም ድንግል ወእም ስትባል መኖሯ አምላክ ወሰብእ ሲባል የመኖሩን ይህንን ታላቅ የሥጋዌ ምሥጢር ያወቅንባት የተረዳንባት መሆኗን ታስረዳለች፡፡

በተጨማሪም ቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና እያለች ከጡቶቿ ወተት ተገኝተው በዝናም አብቅሎ በፀሐይ አብስሎ የሚመግብ መጋቤ ፍጥረታት አምላክን የመገበች፤ እሳታውያን የሚሆኑ ኪሩቤል ሱራፍኤል በፍርሐት በረዐድ በመንቀጥቀጥ ሁነው ዙፋኑን የሚሸከሙት እሳተ መለኮት ጌታን ዘጠኝ ወር ከአምስተ ቀን በማኅፀኗ የተሸከመች፣ በክንዷ የታቀፈች፣ በጀርባዋ ያዘለች፣ እናትነትን ከድንግልና፣ አገልጋይነትን ከእናትነት፣ ወተትን ከድንግልና ጋር አጣምራ የያዘች ምልዕተ ክብር ምልዕተ ጸጋ መሆኗን ዓለም እስከሚያልፍ ድረስ ስትመሰክር ትኖራለች፡፡

**ነገረ ማርያም - ክፍል ፪ (የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም የትውልድ ሀረግ የተቀደሰ ታሪክ)**

**መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ**
**በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሐዲሳት መምህር**

(መቅረዝ ዘተዋሕዶ፣ ታኅሳስ ፪ ቀን፣ ፳፻፮ ዓ.ም):- በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!!

የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እንዳስተማሩትና እንደጻፉት በእናቷ በሐና በኩል ያሉ የእመቤታችን ቅድመ አያቶቿ ጴጥሪቃ ቴክታ ሲባሉ "ወኮኑ ክልኤሆሙ ጻድቃን ወፈራህያነ እግዚአብሔር ወይትአመንዎ ለአምላኮሙ በጥቡዕ ልብ እንበለ ኑፋቄ" ይላል (ኹለቱም ሰዎች ደጋጐችና እግዚአብሔርን የሚፈሩ ያለምንም መጠራጠር በፍጹም ልቡናቸው በአምላካቸው የሚተማመኑ ነበሩ)፤ እነሱም በጊዜው ይኽ ቀራችኑ የማይባሉ ባለጠጎች ነበሩ፤ ከሀብታቸው ብዛት የተነሣ ወርቁን ብሩን እንደ ዋንጫ እያሠሩ ከላሙ ከበሬው ቀንድ ይሰኩት ነበር፤ ይኽን ያኽል አቅርንተ ወርቅ፣ አቅርንተ ብሩር እየተባለ ይቈጠር ነበር የዕንቍ ጽዋ እንኳ ፸፣ ፹ ያኽል ነበራቸው፡፡

ከእለታት ባንዳቸው ጴጥሪቃ ከቤተ መዛግብቱ ገብቶ የሀብቱን ብዛት አይቶ ሚስቱ ቴክታን "ለመኑ ዘዘገብነ መዛግብቲነ አልብነ ውሉድ ዘይወርሰነ አንቲኒ ወአነሂ መካን ንሕነ" (የሰበሰብነው ገንዘብ ስንኳን ለኛ ለልጅ ልጅ ይተርፍ ነበር አንቺም እኔም መካን ነንና የሚወርሰን ልጅ የለንም) በማለት ተናገራት፤ ርሷም እንዲኽ ማለቱ ወላድ የፈለገ መስሏት በሐዘን አምላከ እስራኤል ከኔ ልጅ ባይሰጥኽ ከሌላ ይሰጥኽ ይኾናልና ሌላ አግብተኽ ውለድ አለችው፤ ርሱም "አነሂ ኢይፈቅድ የአምር አምላከ እስራኤል ከመ ኢየሐስቦ ለልብየ" (ይኽንስ እንዳላደርገው በልቤም እንዳላስበው የእስራኤል አምላክ ያውቃል) በማለት ተናገረ፡፡
ርሷም ዐዝና ሳለ ራእይ ታያለች፤ ነጭ እምቦሳ ከማሕፀኗ ስትወጣ እንቦሳዪቱ እንቦሳ እየወለደች እስከ ሰባት ስትደርስ ሰባተኛዋ ጨረቃ፤ ጨረቃ ፀሓይን ስትወልድ አይታ በአድናቆት ለባሏ "ግሩም ግብሩ ለእግዚአብሔር ትማልም ርኢኩ በሕልምየ ጸዐዳ ጣዕዋ ወጽአት እምከርሥየ ይእቲኒ ወለደት ጸዐዳ ጣዕዋ እስከ ሰብዐቲሆን ወሳብእትኒ ወለደት ወርኀ ወወርኀኒ ወለደት ፀሓየ" (የእግዚአብሔር ሥራው ድንቅ ነው፤ ትናንትና ማታ በሕልሜ ነጭ ጥጃ ከማሕፀኔ ስትወጣ ያችም ነጭ ጥጃ ደግሞ ነጭ ጥጃ ስትወልድ እንደዚኽ እየኾነ እስከ ሰባት ትውልድ ሲደርሱ ሰባተኛዪቱ ጨረቃን ስትወልድ ጨረቃዋ ደግሞ ፀሓይን

ስትወልድ አየኍ) በማለት አስረዳችው፤ ርሱም በእጅጉ ተደንቆ ሕልም ከሚፈታ ሰው ዘንድ በመኼድ የሚስቱን ራእይ ነገረው፤ ያም ሕልም ተርጓሚ ምስጢር ተገልጾለት ሰባት አንስት ጥጆች መውለዳችኍ ሰባት ሴቶች ልጆች ይወለዳሉ፤ ነጭ መኾናቸው ደጋግ ልጆች መኾናቸው ሲኾን "ወሳብእትኒ ትከብር እመላእክት ወትትሌአል እምኵሉ ሰብእ ወበእንተ ፀሓይኒ ኢያእመርኩ" (ሰባተኛዪቱ ጨረቃን መውለዷ ከሰው የበለጠች ከመላእክት የከበረች ናት፤የፀሓይ ነገር ግን አልተገለጸልኝም) በማለት ተረጕመለት፤ ርሱም ለሚስቱ ነገራት፤ ርሷም የእስራኤል አምላክ የሚያደርገውን ርሱ ያውቃል በማለት ፈጣሪዋን አመሰገነች። ከዚያም ፀንሳ ሴት ልጅ ወለደች ስሟንም ሔሜን አሏት፤ ሔሜን ዴርዴን ወለደች፤ ዴርዴም ቶናን፤ ቶናም ሲካርን ወለደች፤ ሲካርም ሴትናን፤ ሴትናም ሔርሜላን ወለደች፤ ሔርሜላም የተከበረችና የተመረጠች ዓለሙን ኹሉ ለፈጠረ ጌታ አያት ለመኾን የበቃች ሐናን ወልዳለች፤ የዝማሬና የትንቢት ጸጋ ከእግዚአብሔር የተሰጡት ክቡር ዳዊት ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ክብር በተለይም ስለ ሥርወ ልደቷ፤ አምላክን ስለ መውለዷ፤ አስቀድሞ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾለት በመዝ ፹፮፥፩-፯ ላይ "መሠረታቲሃ ውስተ አድባር ቅዱሳን" (መሠረቶችዋ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው) በማለት የእመቤታችን ሥርወ ልደት ከቤተ መንግሥት ከቤተ ክህነት ከኾኑት ከተቀደሱት ከቅዱሱ ኢያቄምና ከቅድስቲቱ ሐና የመኾኑን ነገር በምሳሌ የገለጸው ሊፈጸም ሐና በመልካም አስተዳደግ አድጋ አካለ መጠን ስታደርስ ከነገደ ይሁዳ ከመንግሥት ወገን ኢያቄም የሚባል ደግና ጻድቅ ሰው ዐጭተው አጋቧት።

ይኽነኑ የሥርወ ልደቷን ነገር በመቅድመ ተአምር ላይ ኢትዮጵያውያን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት "ወሥርወ ልደታ ለእግዝእትነ ማርያም እምቤተ ዳዊት ንጉሥ መንገለ አቡሃ ወእምቤተ አሮን መንገለ እማ፤ ስመ አቡሃ ኢያቄም ወስመ ወላዲታ ሐና" (የእመቤታችን ማርያም ትውልዷ ባባቷ በኩል ከንጉሡ ከዳዊት ወገን ነው፤ በናቷም በኩል ከካህኑ ከአሮን ወገን ነው፤ የአባቷ ስም ኢያቄም ነው፤ የእናቷም ስመ ሐና ነው) ሲል የዘር ሐረግዋ ከቤተ መንግሥት ከቤተ ክህነት ወገን እንደኾነ አስተምረዋል።

ዳዊት ብቻ ሳይኾን ቍጥሩ ከዐበይት ነቢያት መኻከል የኾነው ነቢዩ ኢሳይያስ ጥበብን በሚገልጽ ትንቢትን በሚያናግር በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ፤ ቅድስት ድንግል ማርያም ከነገደ ዕሴይ ወገን የምትወለድ ስለመኾኗና ከርሷም ጽጌ (አበባ) የተባለ አካላዊ ቃል ክርስቶስ እንደሚወለድ ተገልጾለት በምዕ ፲፩፥፩ ላይ "ትወፅእ በትር እምሥርወ ዕሴይ ወየዐርግ ጽጌ እምኔሃ" (ከዕሴይ ሥር በትር ትወጣላች፤ አበባም ከርሷ ይወጣል) በማለት አስደናቂ ትንቢትን ተናግሮ ነበር። በምስጢር የተራቀቀና ከፍተኛ የነገረ ማርያም ዕውቀት የነበረው አባ ጊዮርጊስ ስለ ትውልዷ ኢሳይያስ የተናገረውን ትንቢት በመጽሐፈ ምስጢር ላይ ሲተረጕም

"በከመ ፈቀደ ወአልቦ ዘይከልእ ገቢረ ዘኀለየ በከመ ጽሑፍ ዘይብል ትወፅእ በትር እምሥርወ ዕሴይ ወየዐርግ ጽጌ እምጒንዱ፤ ምንት ውእቱ ፀአተ በትር እምሥርወ ዕሴይ ወየዐርግ ጽጌ እምጒንዱ፤ ምንት ውእቱ ፀአተ በትር እምሥርው ዘእንበለ ዘርዐ ሙላድ ዘቅድስት ድንግል እንተ ኮነት እምኀበ ኢያቄም ውስተ ማሕፀነ ሐና፤ እስመ ዘርዐ ዕሴይ ውእቱ ኢያቄም አቡሃ ለማርያም ወምንትኑመ ካዕበ ዕርገተ ጽጌ እምጒንድ ዘእንበለ ሥጋዌ መለኮት እምወለቱ" (ከዕሴይ ሥር በትር ትወጣለች፤ ከግንዱም አበባ ይወጣል የሚል እንደተጻፈ፤ ያሰበውን ለማድረግ የሚከለክለው የለም፤ ከኢያቄም ተከፍላ በሐና ማሕፀን ከተፀነሰች ከቅድስት ድንግል የትውልድ ዘር በቀር የበትር ከሥሩ መውጣት ምንድን ነው? የእመቤታችን የማርያም አባቷ ኢያቄም ከዕሴይ ዘር ነውና፤ ዳግመኛም ከኢያቄም ሴት ልጁ የመለኮት ሰው መኾን በቀር የአበባ ከግንዱ መውጣት ምንድን ነው) በማለት የኢሳይያስን ትንቢት በጥልቀት ገልጾታል፡፡ ሐናና ኢያቄምንም "ወክልኤሆሙ ኄራን ወሥሙራን እሙንቱ ወየሐውሩ በሕገ እግዚአብሔር እስመ እግዚአብሔር ኀረዮሙ ወአፍቀሮሙ ትካት" ይላቸዋል እግዚአብሔርን የሚወዱ በሕጉ የሚኖሩ ደጋግና አምላክም የመረጣቸው ሲኾኑ ሐና መካን በመኾኗ ምክንያት ኹለቱም ወደ ቤተ እግዚአብሔር ዕለት ዕለት በመኼድ ለዐይናቸው ማረፊያ ለልባቸው ተስፋ የሚኾን ልጅ እንዲሰጣቸው ይማጸኑ እንደነበር፤ "Protoevangelium of James" (ፕሮቶቫንጊሊዩም ኦፍ ጀምስ) የሚለው ያዕቆብ የጻፈው ጥንታዊዉ መጽሐፍ በስፋት ይገልጻል፡፡ ከእለታት ባንድ ዕለት ሲያዝኑ ሲጸልዩ ውለው ሲመለሱ "ወርእዩ አርጋበ እንዘ ይትፌሥሑ ምስለ ውሉዶሙ" ይላል ርግቦች ከልጆቻቸው ጋር ደስ ብሏቸው ሲጫወቱ አይተው ሐና አቤቱ ጌታዬ ግዕዛን ለሌላት እንስሳ ልጅ የሰጠኽ አምላክ ምነው ለኔ ልጅ ነሣኸኝ ብላ ምርር ብላ አለቀሰች፤ ወዲያው ሱባኤ ይገባሉ፤ ኢያቄም በረሓ ኼዶ ወድቋል፤ ሐና ደግሞ ከቤቷ ዙሪያ ካለ ከተክል ቦታ ሱባኤ ያዘች፤ ኹለቱም ራእይ አይተው ተነጋግረዋል፡፡ "ይቤላ ኢያቄም ለሐና ብእሲቱ እንዘ ይትረኀዉ ሰብዐቱ ሰማያት ያፍ ጸዐዳ መጽአ ኀቤየ ወነበረ ዲበ ርእስየ" ይላል ሰባቱ ሰማያት እንደ መጋረጃ ተገልጠው ከላይኛው ሰማይ ነጭ ዖፍ ወርዶ በራሴ ላይ ሲቀመጥ አየኍ ብሎ የተገለጸለትን ለሐና ነግሯታል፤ ይኸውም የራእዩ ምስጢር፡- ዖፍ የተባለው አካላዊ ቃል ክርስቶስ ሲኾን፤ ነጭነቱ ንጽሐ ባሕርዩ ነው፤ ከላይ ወርዶ በራሴ ላይ ሲቀመጥ አየኍ ማለቱ የኢያቄምን ባሕርይ ባሕርይ እንደሚያደርግ ሲያጠይቅ ሲኾን ሰባቱ ሰማያት የተባሉ የጌታችን ምልዐቱ፣ ስፍሐቱ፣ ርቀቱ፣ ልዕልናው፣ ዕበዩ ናቸው፡፡

ሐናም ተገልጾላት "ትቤሎ ሐና ለኢያቄም ብእሴሃ አነኒ ርኢኩ በሕልምየ ርግብ ጸዐዳ መጽአት ኀቤየ ወነበረት ዲበ ርእስየ ወቦአት ውስተ እዝንየ ወኀደረት ውስተ ከርሥየ" ይላል ለባሏ ነጭ ርግብ መጥታ በራሴ ላይ ተቀምጣ ከራሴ ላይ ወርዳ በዦሮዬ ገብቶ በማሕፀኔ ስትተኛ አየኍ ብላዋለች፤ ይኽ የራእይ ምስጢር፡- ርግብ

የተባለች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስትኾን፤ ነጭነቷ ንጽሕናዋ፣ ቅድስናዋ፣ ዘላለማዊ ድንግልናዋ ነው፤ ነጭ ርግብ መጥታ በራሴ ላይ ተቀምጣ ከራሴ ላይ ወርዳ በጕሮሮዬ ገብታ በማሕፀኔ ስትተኛ አየኹ ማለቷ ብሥራተ ገብርኤልን በጕሮሮዋ ሰምታ በግብረ መንፈስ ቅዱስ አምላክን የምትፀንሰውን ንጽሕት ርግብ የተባለችውን እመቤታችንን የምትወልድ መኾኗን ሲያጠይቅ ነው ከነሱም አስቀድሞ የሳሙኤል እናት ሐና በቤተ መቅደስ ኾና "አቤቱ፥ የሠራዊት ጌታ ሆይ፥ የባሪያኽን መዋረድ ተመልክተኽ ብታስበኝ፥ እኔንም ባትረሳ፥ ለባሪያኽም ወንድ ልጅ ብትሰጥ፥ ዕድሜውን ኹሉ ለእግዚአብሔር እሰጠዋለኍ፤ ምላጭም በራሱ ላይ አይደርስም" ብላ ስእለት እንደተሳለች ኹሉ (፩ሳሙ.፩፥፲፩)፤ ኢያቄምና ሐናም ይኽነን ራእይ ሐምሌ ፴ ካዩ በኋላ ወንድ ልጅ ብንወልድ ወጥቶ ወርዶ ይርዳን አንልም ለቤተ እግዚአብሔር አገልጋይ ይኾናል፤ ሴትም ብንወልድ ለቤተ እግዚአብሔር መጋረጃ ፈትላ ትኑር ብለው ስእለት ከተሳሉ በኋላ ራእይ አየን ብለው ዕለቱን አልተገናኙም፤ አዳምንና ሔዋንን "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት" ብሎ የተናገረው አምላክ ለእኛም ይግለጽልን ብለው ዕለቱን አልጋ ምንጣፍ ለይተው እስከ ሰባት ቀን ደረስ እየብቻቸው ሰነበቱ፤ ነሐሴ በባተ በሰባተኛው ቀን ከሰው የበለጠች ከመላእክት ኹሉ የከበረች ልጅ ትወልዳላችኍ ብሎ መልአኩ ለሐና ነግሯት በፈቃደ እግዚአብሔር በብሥራተ መልአክ እመቤታችን ነሐሴ ሰባት እሑድ ተፀንሳለች፡፡

ከሊቃውንት መኻከል አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታ በማሕሌተ ጽጌ መጽሐፋቸው ላይ "ሚ ቡርክት ወቅድስት ይእቲ ሰዓተ ትፍሥሕት ሐና ዘጸገየተኪ ባቲ ወፈረየኪ ለሕይወት ኢያቄም መዋቲ እሴብሕ ተአምረኪ ርግብየ አሐቲ ወድኅኒተ ኵሉ ዓለም እስመ ኮንኪ አንቲ" (ሐና አንቺን የፀነሰችባት የደስታ ቀን ምን ያኽል የተባረከች የተቀደሰች ናት፤ ሟች ኢያቄምም ለሕይወት አንቺን ያፈራባት ቀን ምን ያኽል የተባረከች የተቀደሰች ናት፤ አንዲቱ ርግቤ ማርያም አንቺ የዓለሙ ኹሉ መድኀኒት ኾነሻልና ታምርሽን አመሰግናለኍ) በማለት ዓለምን ኹሉ በደሙ ፈሳሽነት ያዳነ ንጉሣችን፣ ፈጣሪያችን ክርስቶስን በድንቅ ተአምር ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ የወለደችልን ምክንያት ድኂን ርግበ ሰሎሞን የተባለች የቅድስት ድንግልን የመፀነሷን ነገር በአድናቆት ገልጸዋል፡፡ ታላቁ ሊቅ በተለይም ዐምስት የሚኾኑ የነገረ ማርያም መጻሕፍትን የጻፈው አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በአርጋኖን መጽሐፉ ላይ የዜና ጽንሰቷን ነገር ሲገልጽ "ወይእዜኒ ኦ ውሉደ እግዚአብሔር ወማኅበረ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ናስተብፅዖሙ ለሐና ወለኢያቄም ዘወለዱ ለነ ዛተ ቡርክተ ወቅድስተ መርዓተ፤ አይ ይእቲ ዕለት ዕለተ ሩካቤሆሙ ንጽሕት እንተ ባቲ ሐንበበት ፍሬ ቡርክተ ድንግልተ እስራኤል አጽዕልተ፤ አይ ይእቲ ዛቲ ዕለት ቅድስት ዕለተ ድማሬሆሙ ለእሉ በሥምረተ እግዚአብሔር ተገብረ ተፀንሶታ ለርግብ ንጽሕት ዘእምቤተ

ይሁዳ፤ አይ ይእቲ ዕለት ዕለተ ፍሥሐ እንተ ባቲ ኮነ ተመሥርቶ ንድቅ ለማኅፈደ ንጉሥ" (አኹንም የእግዚአብሔር የጸጋ ልጆችና የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ማኅበሮች ሆይ ይኽቺን የተባረከችና የተመረጠች ሙሽራ የወለዱልንን ኢያቄምንና ሐናን እናመስግናቸው የማትነቀፍ የእስራኤል ድንግልን የተባረከችዋን ፍሬ ያፈራችበትን ንጽሕት የምትኾን የሩካቤያቸው ዕለት እንደምን ያለች ዕለት ናት? ከይሁዳ ወገን ለኾነችው ንጽሕት ርግብ መፀነስ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተደረገ የጾታዊ ተዋሕዷቸው ቀን ይኽቺ እንዴት ያለች የተመረጠች ቀን ናት፤ ለንጉሥ ማደሪያ አዳራሽ መመሥረት የተደረገባት (የኾነባት) የደስታ ቀን እንዴት ያላት ቀን ናት?) በማለት አመስግኗታል፡፡

"ወእምድኅረ ስድስቱ አውራኅ ተዐውቀ ፅንሳ ለሐና" ይላል፤ ከስድስት ወርም በኋላ የሐና ፅንሷ እየታወቀ ሲመጣ ጎረቤቶቿ መፅነሷን ይረዱ ዘንድ በአድናቆት ማሕፀኗን ይዳስሱ ነበር፤ በተለይም ዐይኗ የታወረ የሐና ዘመዷ የአርሳባን ልጅ የምትኾን አንዲት ሴት የሐናን ማሕፀን ዳስሳ ዐይኗን ብትነካው በርቶላት በታላቅ ደስታ ኾና "ብጽእን ለኪ ኦ ሐና እስመ እም ፍጥረተ ዓለም አልቦ ዘከማኪ ዘይፌውስ በከርሥ አዕይንተ ዕውራን" (ሐና ሆይ ብጽእን ይገባሻል ዓለም ከተፈጠረ ዠምሮ እንዳንቺ በማሕፀኑ የዕውራን ዐይን የሚያበራ የለምና) በማለት አመስግናታለች፤ ከዚኽ በኋላ ዝናዋ በሀገሩ ኹሉ ተሰምቶ ሕሙማን ኹሉ ማሕፀኗን እየዳሰሱ ይፈወሱ ነበር፡፡

በመቶ ሃምሳ መዝሙረ ዳዊት ልክ መቶ ሃምሳ ክፍል ያለው የእመቤታችንን ምስጋና የጻፉት አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታ በማሕሌተ ጽጌ መጽሐፋቸው ላይ ይኽነን ሲገልጹ "ጸግይየ ሣዕረ ዘኪሩቤል ልሳነ ተአምረኪ በነጊር እመ ኢፈጸምኩ አነ ባሕቱ አአኰት ማርያም ዘጾረተኪ ማሕፀነ እንዘ ሀለወት ፀኒሳ ኪያኪ ርጢነ ለለገሠሥዋ ባቲ ትፌውስ ዱያነ" (ሳር የኾንኊ እኔ የኪሩቤልን አንደበትን ገንዘብ አድርጌ ታምርሽን በመንገር በማስተማር ባልፈጽምም፤ ነገር ግን ማርያም የተሸከመቺሽን ማሕፀን አመሰግናለኊ፤ መድኀኒት አንቺን ፀንሳ ሳለች ርሷን የዳሰሷትን ድዉያንን ኹሉ ትፈውስ ነበር) በማለት እመ መድኅነ ዓለም ገና ሳትወለድ የተሠራውን ድንቅ ተአምር አመስግነዋል፡፡

በእጅጉ የሚደንቀው ደግሞ ሳሚናስ የሚባል የጦሊቅ ልጅ ከኤዶቅ ካጕቱ ቤት ኼዶ ሞተ፤ ሐናም በሀገራቸው ልማድ የአልጋውን ሸንኮር ይዛ እየዞረች ስታለቅስ ጥላዋ ቢያርፍበት መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል ፈጥኖ ተነሥቶ "ሰላም ለኪ ኦ ሐና ወእምሔውቱ ለዘገብረ ሰማየ ወምድረ" (ሰማይና ምድርን ለፈጠረው አምላክ አያቱን የተባልሽ ሐና ሰላም ላንቺ ይኹን) አላት፤ ከዚያ የነበሩ አይሁድም በመደናገጥ ሳሚናስ ምን አየኽ? ምን ትላለኽ? አሉት፤ ርሱም ከዚች ከሐና

ማሕፀን የምትወለደው ሕፃን ሰማይ ምድርን የፈጠረ አምላክን ትወልዳለች እያሉ መላእክት ኹሉ ሲያመሰግኗት ሰማኂቸው፤ እኔንም ያነሣችኝ ርሷ ናት አላቸው፤ እነርሱም ይኽን በሰሙ ጊዜ እግዚአብሔርን ከማመስገን ይልቅ በቅናትና በክፋት ተመልተው ሐና በማሕፀን ሳለ ካዳነች በኛ ላይ ልትሠለጥን አይደል “ንዑ ንገሮሙ ለሐና ወለኢያቄም” ሳትወልድ አስቀድመን ሐናና ኢያቄምን በድንጋይ ወግረን እንግደላቸው ብለው ተነሣሡባቸው፤ ያን ጊዜ ታላቁ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ለኢያቄም ተገልጾ ሐናን ሊባኖስ ወደሚባል ተራራ እንዲወስዳት ነገረው፤ ጠቢቡ ሰሎሞን በመንፈሰ እግዚአብሔር ተቃኝቶ እመቤታችን በሊባኖስ ተራራ እንደምትወለድ ተገልጾለት “ንዒ እምሊባኖስ መርዓት ንዒ እምሊባኖስ ንዒ ወተወፅኢ እምቅድመ ሃይማኖት እምርእሰ ሳኔር ወኤርሞን እምግበበ አናብስት ወእምአድባረ አናምርት” (ሙሽራዬ ሆይ ከሊባኖስ ከእኔ ጋር ነዪ ከሊባኖስ ከእኔ ጋር ነዪ ከአማና ራስ ከሳኔር ከኤርሞን ራስ ከአንበሶች መኖሪያ ከነብሮችም ተራራ ተመልከች) በማለት የተናገረው ትንቢት ሊፈጸም ቅድስት ድንግል ማርያም በ፭ ሺሕ ፬፻፹፭ ዓመተ ዓለም በሊባኖስ ተራራ ተወልዳለች (ማሕ ፬፥፲)። ኢትዮጵያዊ ቄርሎስ የተባለው የነገረ ማርያም ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እመቤታችን በሊባኖስ እንደምትወለድ አስቀድሞ ሰሎሞን የተናገረው ቃል መፈጸሙን ሲገልጽ “ወካዕበ እሰምየኪ ወለተ አናብስት እስመ ከመ ጣሕረ አንበሳ ወንቃወ አንበሳዊት ይደምፅ ዜና ልደትኪ እስመ ለይሁዳ ይቤሎ አቡሁ ያዕቆብ ዕጓለ አንበሳ (ዘፍ ፵፱፥፱) ፤ ወበእንተዝ ሰመይኩኪ ወለተ አናብስት በከመ ይቤ ሰሎሞን ንዒ እምሊባኖስ መርዓት ንዒ ወትወፅኢ እምግበበ አናብስት (ማሕ ፬፥፲) ጥቀ ግሩም ዜና ልደትኪ እምሕዝብ ዘይትሜካሕ ወእምነገድ ኅሩይ” (ዳግመኛም የአንበሶች ልጅ ነሽ እልሻለኍ፤ የልደትሽ ዜና እንደ አንበሳ ጩኸት እንደ ሴት አንበሳ ድምፅ ነውና፤ ይሁዳን አባቱ ያዕቆብ የአንበሳ ግልገል ብሎታልና (ዘፍ ፵፱፥፱)፤ ስለዚኽም የአናብስት ልጅ አልኹሽ ሰሎሞን እንዲኽ ሲል እንደተናገረ ሙሽራዬት ሆይ ከሊባኖስ ተራራ ነዪ ከአንበሶች ጉድጓድ ወጥተሽ ነዪ (ማሕ ፬፥፲) ከምርጥ ነገድነት የተነሣ ከሚመካ ወገን የመወለድሽ ዜና እጅግ ግሩም ነው) በማለት አመስጥሮታል።

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታ በማሕሌተ ጽጌ የነገረ ማርያም መጽሐፋቸው ላይ “ለንጉሠ ነገሥት ሰሎሞን ከመ ተፈሥሐ ልቡ በዕለተ ወፃእኪ መርዓት ለአንበሳ ትንቢት እምግቡ ማእከለ ማኅበር ፍሱሓን ተአምረኪ እንዘ እነቡ እዜምር ለኪ ጽጌ ሐና ወፍኖተ ነፈርዐጽ እሌቡ ከመ ጣዕዋ ሐሊበ ዘይጠቡ” (ትንቢት ከተነገረለት ከአንበሳ ጉድጓድ፤ ድንግል ሙሽራ በተገኘሽ ጊዜ የንጉሦች ንጉሥ የሰሎሞን ልቡ እንደተደሰተ፤ ደስ ባላቸው በመላእክት አንድነት ፊት ታምርሽን እየተናገርኍ የሐና አበባ ማርያም እዘምርሻለኍ፤ ወተትን ጠብቶ እንደሚዘል እንቦሳም ዝለል ዝለል ይለኛል) በማለት ሰሎሞን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ልደት የተናገረው ትንቢት

ፍጻሜውን አግኝቶ ታላቅ ደስታን ለኹላችን እንደሰጠን አብራርተው ገልጠዋል። ይኽ የእመቤታችን ልደት ለሰማያውያን መላእክትና ለደቂቀ አዳም ደስታ ሲኾን አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከርሷ ተወልዶ ዲያብሎስ ፭ሺሕ፭፻ ዘመን በሲኦል ያኖራቸውን ነፍሳት ወደ ገነት የሚያስገባቸው ነውና፤ ሰይጣን በተቃራኒው ልደቷ እንዳላስደሰተው ሲገልጹ "ተፈሥሐተ ምድር ወሰማይ አንፈርዐፀ በዕለተ ጸገዩኪ አብላስ ወአውጽኡ ሠርፀ ተአምረ ሕይወት ማርያም ዘአልብኪ ቢጸ እስከ ፈርሀ መልአከ ሞት ወሰይጣን ደንገጸ ዜና ልደትኪ ነጐድጓድ እስከ (ውስተ) ሲኦል ደምፀ" (በለሶች (ኢያቄምና ሐና) ቡቃያ አንቺን ባስገኙሽ ጊዜ ምድር ደስ አላት ሰማይም ደስ አለው፤ ጓደኛ (ምሳሌ) የሌለሽ የድኅነት ምልክት ማርያም፤ መልአከ ሞት እስከ ፈራና ሰይጣንም እስከ ደነገጠ ድረስ የመወለድሽ ዜና እስከ ሲኦል ድረስ (በሲኦል) ተሰማ) በማለት አስተምረዋል።

ጠቢቡ ሰሎሞን አስቀድሞ በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ በማሕልዩ ላይ "መኑ ይእቲ ዛቲ እንተ ትሔውጽ ከመ ጎሕ ሠናይት ከመ ወርኅ ወብርህት ከመ ፀሓይ" (ይኽቺ እንደ ማለዳ ብርሃን የምትጐበኝ እንደ ጨረቃ የተዋበች፤ እንደ ፀሓይም የጠራች ዐላማ ይዞ እንደተሰለፈ ሰራዊት የምታስፈራ ማን ናት?) በማለት እንደ ፀሓይ የሞቀ እንደ ጨረቃ የደመቀ ንጽሕናዋና ቅድስናዋ የመልካ ደም ግባት በነቢያት ትንቢት አስቀድሞ የተጐበኘላት የእውነት ፀሓይ የክርስቶስ እናት የቅድስት ድንግል ማርያምን ክብርና ደም ግባቷን እንደተናገረ በሊባኖስ ተራራ በግንቦት ፩ በተወለደች ጊዜ ፊቷ እንደ ፀሓይ ያበራ ነበር፤ መዐዛዋም ከሽቱ ኹሉ ይበልጥ ነበር።

የመዐዛዋን ድንቅነት ይኸው አባት ሰሎሞን መንፈስ ቅዱስ ገልጾለት ይኽነንም በተለያዩ ድንቅ መዐዛ ባላቸው ሽቱዎች መስሎ ሲናገር (ቡቃያሽ ሮማንና የተመረጠ ፍሬ ቆዕ ከናርዶስ ጋር ያለበት ገነት ነው፤ ናርዶስ ከቀጋ ጋር የሽቱ ሣርና ቀረፋ ከልዩ ልዩ ዕጣን ጋር፤ ከርቤና እሬት ከክቡር ሽቱ ኹሉ ጋር አንቺ የገነት ምንጭ የሕይወት ውሃ ጉድጓድ ከሊባኖስም የሚፈስስ ወንዝ ነሽ) በማለት የሕይወት ውሃ የክርስቶስ እናቱ በሊባኖስ የተወለደቺው የቅድስት ድንግል ማርያምን ልዩና ድንቅ መዐዛ ተናግሯል።

ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ ቅዱስ ያሬድም የመዐዛዋን አስደናቂነት በሰሎሞንን ቃል በአንቀጸ ብርሃን መጽሐፉ ላይ ሲገልጸው (አባትሽ ሰሎሞን ያፍንጫሽ መዐዛ እንደ ነጭ ዕጣን መዐዛ ነው ብሎ ትንቢት ተናገረ፤ እቴ ሙሽራዬ ሆይ የታጠርሽ ተክል ነሽ፤ መንገድሽም የታጠረች ተክል የታተመች ጉድጓድ ናት፤ ከሽቱ ቅመም ጋራ ሽቱ አለሽ፤ ቆዕ የሚባል ሽቱ ናርዶስ ከሚባል ሽቱ ጋር አለሽ፤ ናርዶስ የሚባል ሽቱ መጽርይ ከሚባል ሽቱ ጋር አለሽ፤ ቀጺመታት ቀናንሞስ የሚባሉ ሽቶች ከደጋ ሽቶች ጋር አሉሽ፤ ከሽቶች ኹሉ የሚበልጡ ከርቤና ዐልው የሚባሉ

ሽቶች ከነዚኽ ኹሉ ሽቶች ጋር አሉሽ፤ የገነት ፈሳሽ ሆይ ከደጋ የሚፈስስ የሕይወት ውሃ ጉድጓድ ነሽ) በማለት የመዐዛዋን ነገር አድንቋል። የእመቤታችን ጣዕመ ውዳሴዋ በእጅጉ የበዛለት ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በአርጋኖን ምስጋናው ከሰሎሞን ቃል በመነሣት የመዐዛዋን ነገር ሲያደንቅ "ወእወዲ ውስተ አፋየ እምፍሬ ከርሥኪ ጥዑም ለጉርዔየ ደመ አስካልኪ ወመድምም ለአንፍየ መዐዛ ዕፍረትኪ ከመ ዘሰትየ ወይነ ከራሜ ያስተፌሥሖ ለልብየ ስብሐተ ድንግልናኪ ሚመጠን ፍሥሓየ በእንቲኣኪ ወሚመጠን ሐሤትየ በእንተ ክብርኪ አዳም ንባብኪ ወመዓርዒር ቃልኪ ሙሐዘ ፍሥሐ ከናፍርኪ ወሙሒዘ ስብሐት ልሳንኪ ጥቀ ሠነይኪ ወጥቀ አደምኪ አፈቅሮ ለፍግዕኪ ዘቆምኪ ይመስል በቀልተ ወጼና አልባስኪ ከመ ርሔ አፈው ወጼና አንፍኪ ከመ ጼና ወይን (ማሕ ፯፥፯-፰) ወመክሥተ አፉኪ ምዑዝ ከመ ጼና ጽጌ ቀናንሞስ ዘምስለ ኵሉ ዕፀወ ሊባኖስ" (ከማሕፀንሽም ፍሬ ወደ አፌ እጨምራለኍ፤ የፍሬሽ ደምም ለጉሮሮዬ የጣፈጠ ነው፤ የሽቱሽ መዐዛም ለአፍንጫዬ ያማረ ነው፤ የድንግልናሽ ክብርም ልቡናዬን እንደ ከረመ ንጹሕ ወይን ደስ ያሰኘዋል፤ ስለ አንቺ ያለኝ ደስታ ምን ያኽል ነው፤ አነጋገርሽ ያማረ ነው፤ ቃልሽም የጣፈጠ ነው፤ ከንፈሮችሽም የደስታ ምንጭ ናቸው፤ አንደበትሽም የምስጋና መፍለቂያ ነው፤ እጅግ በጣም አማርሽ ቁመትሽ የሰሌን ዛፍ፤ የልብሶችሽ መዐዛም አፈው በመባል እንደሚታወቀው ሽቱ፤ የአፍንጫሽ መዐዛም እንደ ወይን አበባ ሽታ የሚኾንልሽ ድንግል ሆይ ደስታሽን እወደዋለኍ (ማሕ ፯፥፰) የአፍሽም አከፋፈት እንደ ቀናንሞስ አበባ የጣፈጠ ነው፤ ከሊባኖስ ዕንጨቶች ኹሉ ጋር (ማሕ ፬፥፲፬)) በማለት እንደ ሰሎሞን ርሱም የፈጣሪውን እናት አመስግኗል።ሐናና ኢያቄምም በእጅጉ ተደስተው በተወለደች በ፰ ቀኗ ስሟን ማርያም ብለው ሰየሚት።

**ነገረ ማርያም - ክፍል ፫ (የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ቤተ መቅደስ መግባት)**

**በመጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ**
**በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሐዲሳት መምህር**

**(መቅረዝ ዘተዋሕዶ፣ ታኅሳስ ፫ ቀን፣ ፳፻፮ ዓ.ም.)፡- በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!!**

**ቅድስት ድንግል ማርያምም እስከ ሦስት ዓመት ድረስ በእናት በአባቷ ቤት ውስጥ ኖራለች፤ ይኽነን በእናት በአባቷ ቤት የነበራትን አስተዳደግ "Protoevangelium of James" (ፕሮቶቫንጊሊዩም ኦፍ ጀምስ) በሚለው ጥንታዊዉ መጽሐፍ ሲገልጽ (ሕፃኗም ከቀን ወደ ቀን በኀይልና በብርታት እያደገች ኼደች፤ የስድስት ወር ልጅ በኾነች ጊዜ እናቷ መቆም ትችል እንደኾነ ለማየት መሬት ላይ አቆመቻት፤ ርሷም ሰባት ርምጃ ተራምዳ ወደእናቷ ዕቅፍ ውስጥ ገባች፤ እናቷም እንዲኽ አለቻት "ወደ ጌታ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አስክወስድሽ ድረስ በራስሽ እንዳትራመጂ አለቻትና በመኝታ ቤቷ ውስጥ ውስጥ የቅድስና ስፍራ አበጀችላት… አንድ ዓመት በኾናት ጊዜም ኢያቄም ታላቅ ግብዣ አድርጎ ካህናቱን፣ ጸሐፊትን፣ ታላቆችንና ሕዝብን ጠራ፤ ከዚያም ኢያቄም ልጁን ወደ ካህናቱ አቀረባት እነርሱም "አባታችን እግዚአብሔር ሆይ ይኽቺን ልጅ ባርካት በትውልድ ኹሉ የሚጠራ ማብቂያ የሌለው ስምን ስጣት እያሉ ባረኳት፤ ሕዝቡም ኹሉ "ይደረግ ይኹን ይጽና አሜን" አሉ፤ ከዚያም ወደ ሊቀ ካህናቱ ወሰዳት ርሱም "ልዑል እግዚአብሔር ሆይ ይኽቺን ልጅ ተመልከት ለዘላለም በሚኖር በፍጹም በረከትም ባርካት" በማለት ባረካት፤ ሐናም ይዛት ወደ ተቀደሰው የማደሪያዋ ክፍል በመውሰድ ጡትን ሰጠቻት…) ይላል።**

**ከዚኽ በኋላ እናቷ ሐና ልጇ ሦስት ዓመት በኾናት ጊዜ ጠቢቡ ሰሎሞን በመጽሐፈ መክብብ ምዕ ፭፥፬-፭ ላይ "ሰነፎች ደስ አያሰኙትምና ለእግዚአብሔር ስእለት በተሳልኽ ጊዜ ትፈጽመው ዘንድ አትዘግይ የተሳልኸውን ፈጽመው፤ ተስለኽ የማትፈጽም ብትኾን ባትሳል ይሻላል" ብሎ የተናገረውን በማሰብ ባሏ ኢያቄምን ይኽቺ ብላቴና የብጽአት ገንዘብ እንደኾነች ታውቃለኽ ወስደን ለቤተ እግዚአብሔር እንስጣት አለችው፤ ርሱም ፍቅርሽ ይለቅልሽ ብዬ ነው እንጂ እኔማ ፈቃዴ ነው አለ፤ ኢያቄም ይኽነን ማለቱ ሐና እመቤታችንን በመካንነት ኑራ ያገኘቻት አንድያ ልጇ ናትና ከፍቅሯ ጽናት የተነሣ ተለይታት አታውቅም ነበርና ነው።**
**ጥበብ ሥጋዊ ጥበብ መንፈሳዊ በእጅጉ የተሰጠው ሰሎሞን አስቀድሞ በመንፈሰ እግዚአብሔር በመቃኘት የሐና አንድያ ልጇ የኾነቺው በየዋህነቷ በርግብ**

የተመሰለች ቅድስት ድንግል ማርያምን ስፍር ቍጥር ከሌላቸው ከሌሎች ሴቶች ተለይታ ለአምላክ እናትነት ብቸኛ ተመራጭ መኾኗን በማሕ ፮፥፰-፲ ላይ "አዋልድ እለ አልቦን ኍልቍ" (ቍጥር የሌላቸው ቆነዣዥት አሉ) በማለት ስፍር ቍጥር የሌላቸው እጅግ የበዙ ሴቶች መኖራቸው ከተናገረ በኋላ "አሐቲ ይእቲ እምኔሆን ርግብየ ፍጽምትየ" (ርግቤ መደምደሚያዬ አንዲት ናት) ብሎ ከነዚያ ኹሉ ተለይታ በየዋህነቷ በርግብ የተመሰለችው ቅድስት ድንግል ብቸኛ እናት ትኾነው ዘንድ በአምላክ የመመረጧን ነገር ከተናገረ በኋላ "አሐቲ ይእቲ ለእማ ወኅሪት ይእቲ ለእንተ ወለደታ" (ለእናቷ አንዲት ናት፤ ለወለደቻትም የተመረጠች ናት) በማለት እናቷ ቅድስት ሐና በመካንነት ከኖረች በኋላ የወለደቻት ምርጥ ልጇ መኾኗ ተገልጾለት ተናግሯል።

ከዚኽ በኋላ ዳዊት በመዝ ፳፮፥፬፤ ፵፩፥፰፤ ፻፲፰፥፲፰-፲፱ ላይ "እግዚአብሔር በቀን ቸርነቱን ያዝዛል በሌሊትም ዝማሬው በእኔ ዘንድ ይኾናል የእኔ ስእለት ለሕይወቴ አምላክ ነው…በሕዝቡ ሁሉ ፊት ስእለቴን ለእግዚአብሔር እፈጽማለሁ በእግዚአብሔር ቤት አደባባይ ኢየሩሳሌም ሆይ በመካከልሽም ሃሌሉያ… እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት እርስዋንም እሻለሁ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ፥ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውንም አይ ዘንድ፥ መቅደሱንም እመለከት ዘንድ … " በማለት እንደተናገረ ኢያቄምና ሐና እግዚአብሔርን በማመስገን ካህኑ ዘካርያስን "ይኽቺ ብላቴና ተስለን አምላካችን በቸርነቱ የሰጠን ናትና ተቀበለን" አሉት ርሱም ቢያያት እንደ ፀሓይ የምታበራ እንደ መብረቅ ግርማዋ የሚያስፈራ የምታበራ ዕንቈ ባሕርይ መስላ ታየችው። ርሱም በአድናቆት ይኽቺን የመሰለች ፍጥረት ምን እናደርጋታለን፣ ምን እናበላታለን፣ ምንስ እናጠጣታለን፣ ምን እናነጥፍላታለን፣ ምን እንጋርድላታለን ብሎ ሕዝቡን ሰብስቦ ሲጨነቁ ለእስራኤል ደመና ጋርዶ መናን አውርዶ የመገበ፤ ለኤልያስም በመልአኩ እጅ በመሶበ ወርቅ ኅብሥት የመገበ፤ ለዕዝራ ሱቱኤልም በመልአኩ በቅዱስ ዑራኤል እጅ መልኩ እሳት የሚመስል ጽዋዐ ልቡና ያጠጣው ልዑል እግዚአብሔር ለእናትነት ወደ መረጣት ወደ እናቱ መልአኩ ፋኑኤልን ላከላት (ዘፀ ፲፮፥፴፩፤ ፩ነገ ፲፱፥፮፤ ዕዝ. ሱቱ. ፲፫፥፴፰-፵፩)።

ይኽም ፋኑኤል የተባለው መልአክ ቍጥሩ ከሰባቱ ሊቃነ መላእክት አንደኛው ሲኾን ሐዋርያው ይሁዳ ከቍ፲፬-፲፭ ላይ ስለመጽሐፉ የጠቀሰለት የአዳም ሰባተኛ ትውልድ የኾነው ሞትን ሳያይ የተሰወረው ታላቁ አባት ሔኖክ በምዕ ፲፥፲፭ ላይ "አራተኛው የዘላለም ሕይወት የሚወርሱ ሰዎች ተስፋ ሊኾን ንስሐ በሚገቡ ሰዎች ላይ የተሾመ ፋኑኤል ነው" በማለት የመልአኩን ክብር መስክሮለታል። "ወሶቤሃ ወረደ ፋኑኤል ሊቀ መላእክት ወጸለላ በአክናፊሁ ወተለዐለ ላዕለ መጠነ ቆመ ብእሲ ወወሃባ ወመጠዋ ወዐርገ ውስተ ሰማይ" ይላል በዚያን ጊዜ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ፋኑኤል ኅብስት ሰማያዊ በብርሃን ጽዋዕ ስቴ ሕይወት ይዞ ረቦ

ወረደ፤ ዘካርያስ ለርሱ የመጣ ሀብት መስሎት ሊቀበል ቢነሣ ወደ ላይ ሰቀቀበት፤ ያን ጊዜ ጥበበ እግዚአብሔር አይመረመርምና ለዚኽች ብላቴና የመጣ ሀብት ይኾናል እስኪ እልፍ አድርጋችኊ አኑሯት አለ፤ እልፍ አድርገው ቢያኖሯት ድንኩል ድንኩል እያለች እናቷን ስትከተል መልአኩ አንድ ክንፉን አንጽፎ አንዱን ክንፉን አጕናጽፎ ከመሬት የሰው ቁመት ያኽል ከፍ ብሎ ኅብስቱን መግቧት ጽዋውን አጠጥቷት ወደ ሰማይ ዐርጓል፡፡

አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታ በማሕሌተ ጽጌ የነገረ ማርያም መጽሐፋቸው ላይ በመልአኩ እጅ የመመገቧን ነገር ሲገልጹ "የሐዘነኒ ማርያም ዘረከበኪ ድክትምና አመ ቤተ መቅደስ ቦእኪ እንዘ ትጠብዊ ሐሊበ ሐና ወያሥተፌስሐኒ ካዕበ ትእምርተ ልሕቀትኪ በቅድስና ምስለ አብያጺሁ ከመ አብ እንዘ ይሴስየኪ መና ፋኑኤል ጽጌ ነድ ዘይከይድ ደመና" (ማርያም የሐናን ወተት እየጠባሽ ወደ ቤተ መቅደስ በገባሽ ጊዜ ያገኘሽ ብቸኝነት ያሳዝነኛል፤ ዳግመኛም በደመና የሚመላለስ ደመናን የሚረግጥ የእሳት አበባ ፋኑኤል ከጓደኞቹ መላእክት ጋር መናን እየመገበሽ በንጽሕና የማደግሽ ተአምር ደስ ያሰኘኛል) በማለት አመስግነዋል፡፡

ካህናቱም ሕዝቡም የምግቧማ ነገር ከተያዘ ከሰው ጋራ ምን ያጋፋታል ቦታዋ ከቤተ መቅደስ ይኹን እንጂ ብለው ዙፋኑን ዘርግተው፣ ምንጣፉን አንጥፈው፣ ግራና ቀኝ መጋረጃውን ጋርደው ነቢዩ ዳዊትም በመዝ 41፡4 ላይ "ወደ እግዚአብሔር ቤት ወደ ምስጋና መኖሪያ ስፍራ እገባለሁና በዓል የሚያደርጉ ሰዎች የደስታና ምስጋና ቃል አሰሙ" በማለት እንደተናገረ ስላዩትና ስለተደረገው ነገር ኹሉ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ አማናዊት የአምላክ መቅደስ የአካላዊ ቃል ታቦት እመቤታችንን ወደ ቤተ መቅደስ በ፳ሺሕ ፬፻፹፯ ዓመተ ዓለም በሦስት ዓመቷ አስገቧት፡፡

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከእናቷ ከአባቷ ቤት ተለይታ በእግዚአብሔር ቤት በቤተ መቅደስ እንደምታድግ ነቢዩ ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ ተገልጾለት በመዝ ፵፬፥፱-፲፩ ላይ "በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች ልጄ ሆይ፥ ስሚ እዪ ጆሮሽንም አዘንብዪ ወገንሽን ያባትሽንም ቤት እርሺ ንጉሥ ውበትሽን ወድዶአልና፥ እርሱ ጌታሽ ነውና" በማለት የተናገረው ትንቢት ሊደርስ ሊፈጸም አማናዊት መቅደስ ርሷ ምሳሌዋ ወደሚኾነው ቤተ መቅደስ እንድትገባ ባለቤቱ አድርጓል፡፡ በቤተ መቅደስ ውስጥ በንጽሕናና እግዚአብሔርን እያገለገሉ ስለማደግና ስለመኖር መጽሐፍ ቅዱስ በስፋት ሲገልጽ ከዚኽ ውስጥ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከተወለደ በኋላ በስለት ተሰጦ የእግዚአብሔር አገልጋይ ኾኖ በቤተ መቅደስ ያደገው ሳሙኤል ሲጠቀስ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ደግሞ ከአሴር ወገንም የነበረችው

የፋኑኤል ልጅ ነቢይት ሐና ከድንግልናዋ ጀምራ ከባልዋ ጋር ሰባት ዓመት ከኖረች በኋላ ሰማኒያ አራት ዓመት ያህል መበለት ኾና በጣም አርጅታ ሳይቀር በጾምና በጸሎትም ሌሊትና ቀን እያገለገለች ከመቅደስ አትለይም እንደነበር ተጽፎ እናነባለን (፩ሳሙ ፪÷፲፰፤ ሉቃ ፪÷፴፮-፴፯)፡፡

አማናዊት የአምላክ መቅደስ እመቤታችንም ምሳሌዋ በኾነ በቤተ መቅደስ ከገባች ዝምሮ መላእክት እያረጋጓት ካህናት እያመሰገኗት ኅብስተ ሰማያዊ እየመገቧት ጽዋዕ ሰማያዊ እያጠጧት ለዐሥራ ኹለት ዓመት ያኽል በቤተ መቅደስ ስለመቀመጧ በ፭፻፭ (505) ዓ.ም የተወለደው ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያሬድም በአንቀጸ ብርሃን የነገረ ማርያም መጽሐፉ ላይ ሲገልጽ፡- "አንቲ ውእቱ ንጽሕት እም ንጹሓን ድንግል ኅሪት ዘነበርኪ ውስተ ቤተ መቅደስ ከመ ታቦት ዘግቡር እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ሥርግው በወርቅ ንጡፍ ወልቡጥ በዕንቊ ባሕርይ ዘየሐቱ ዘብዙኅ ሤጡ ከመዝ ነበርኪ ውስተ ቤተ መቅደስ ወመላእክት ያመጽኡ ወትረ ሲሳየኪ ከመዝ ነበርኪ ፲ተ ወ፪ተ ዓመተ እንዘ ትትናዘዚ እምኅበ መላእክት ስቴኪኒ ስቴ ሕይወት…" (ከንጹሓን ይልቅ ንጽሕት የኾንሽ አንቺ ነሽ፤ ከማይነቅዝ ዕንጨት እንደተሠራ በወርቅ እንደተጌጠና ዋጋው ብዙ በኾነ በሚያበራ ዕንቍ እንደተለበጠ ታቦት በቤተ መቅደስ ውስጥ የኖርሽ የተመረጥሽ ድንግል ነሽ፤ እንዲኽ ኾነሽ በቤተ መቅደስ ውስጥ ኖርሽ፤ መላእክት ዘወትር ምግብሽን ያመጡ ነበር፤ መላእክት እየጐበኙሽ እንዲኽ ዐሥራ ኹለት ዓመት ኖርሽ፤መጠጥሽም የሕይወት መጠጥ ነበር፤ ምግብሽም የሰማይ ኅብስት ነበር፤ አባትሽ ዳዊት በመሰንቆ አመሰገነ በትንቢት መንፈስም በመንፈስ ቅዱስ በገና እየደረደረ እንዲኽ ብሎ ዘመረ፤ ልጄ ሆይ ስሚ እዩም ዡሮሽንም አዘንብዪ ሕዝብሽንና የአባትሽን ቤት ርሺ፤ ንጉሥ ደም ግባትሽን ወዷልና፤ ርሱ ጌታሽ ነው፤ ለርሱ ትሰግጃለሽ (መዝ ፵፬)) በማለት በቤተ መቅደስ በነበረችበት ወቅት የተደረገውን ተአምራት አድንቋል፡፡

ሊቁ አባ ሕርያቆስም በተመሳሳይ መልኩ በቅዳሴ ማርያም መጽሐፉ ላይ (ድንግል ሆይ አንገታቸውን እንደሚያገዝፉ እንደ ዕብራውያን ሴቶች ልጆች በዋዛ ያደግሽ አይደለም፤ በንጽሕና በቅድስና በቤተ መቅደስ ኖርሽ እንጂ፤ ድንግል ሆይ ምድራዊ ኅብስትን የተመገብሽ አይደለሽም፤ ከሰማየ ሰማያት የበሰለ ሰማያዊ ኅብስትን ነው እንጂ፤ ድንግል ሆይ ምድራዊ መጠጥን የጠጣሽ አይደለሽም፤ ከሰማየ ሰማያት የተቀዳ ሰማያዊ መጠጥን ነው እንጂ፤ ድንግል ሆይ ከአንቺ አስቀድሞ ከአንቺም በኋላ እንዳሉ ሴቶች ዕድፍን የምታውቂ አይደለሽም፤ በንጽሕና በቅድስና ያጌጥሽ ነሽ እንጂ፤ ድንግል ሆይ የሚያታልሉ ጐልማሶች ያረጋጉሽ አይደለሽም የሰማይ መላእክት ጐበኙሽ እንጂ እንደተነገረ ካህናትና የካህናት አለቆች አመሰገኑሽ እንጂ) በማለት እመቤታችን በቤተ መቅደስ በነበረችበት ዐሥራ ኹለት ዓመታት የተደረገላትን ድንቅ ሥራ ገልጾታል፡፡ እመቤታችን ወደ ቤተ መቅደስ እንዴት እንደገባችና በቤተ መቅደስ ውስጥ

የነበራትን ቆይታ ቀደምት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በጥልቀት ጽፈዋል፤ ከእነዚኽ መኻከል ሊቁ የቆጵሮሱ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ የቤተ መቅደስ ቅድስናዊ አኗኗሯን ሲጽፍ “She was grave and dignifified in all her action…” (እመቤታችን በኹሉም እርምጃዎቿ ጉበዝና የተከበረች ነበረች፤ የምትናገረው በጣም ጥቂት ሲኾን ርሱም ለማድረግ አስፈላጊ በሚኾንበት ብቻ ነበር፤ በጣም ዝግጁ ኾና የምትሰማና በቀላሉ ንግግር ለማድረግ የምትችል ናት፤ ለእያንዳንዱ ሰው አክብሮትና ክብር (ሰላምታ) ትሰጣለች፤ ቁመቷ መኻከለኛ ሲኾን አንዳንዶች ግን ቁመቷ ከፍ ያለ እንደነበር ይናገራሉ፤ ከእያንዳንዱ ሰው ጋር ያለምንም ፍርሃት በግልጽነት ያለምንም ሳቅና መጯጯኽ ትናገራለች፤ በተለይ ፈጽማ ለቁጣ የምትጋበዝ አልነበረችም፤ መልኳ እንደ ደረሰ የስንዴ አዝመራ ያማረ ጸጉሯ ቀይማ ነው፤ ዐይኖቿ ብሩሃትና የዋህ የኾኑ ቀለማቸውም ፈዘዝ ያለ ቡናማ ኾኖ የዐይኖቿ ብሌኖች የዘይት-አረንጓዴ ይመስላል፤ የዐይኖቿ ቅንድብ (ሽፋሽፍት) ከፊል ክብና ደማቅ ጥቁር ናቸው፤ አፍንጯዋም ረዥም፣ ከናፍሮቿ ቀይና ምሉዕ ሲኾኑ በቃላቷ ጣፋጭነት የተጥለቀለቁ ነበሩ፤ ፊቷ ክብ ሳይኾን ግን እንቁላልማ ዐይነት ቅርጽ ነበረው፤ እጆቿ ረዥምና ጣቶቿም በጣም ረዣዥም ነበሩ፤ ከማንኛውም ያልተገባ ኵራት ሙሉ በሙሉ የነጻች ስትኾን ግድ የለሽነት ፈጽሞ ጨርሶ የለባትም ነበር፤ የሚመጡትን ነገራት በፍጹም ትሕትና ትቀበል ነበር፤ ተፈጥሯዊ ቀለማት ያላቸው (ማለትም በቤት ድር የተሠሩ) ልብሶችን ታረግ ነበር፤ ይኽም በእጅጉ አብሯት የሚኼደው አለባበስና ይኽ እውነታ በራሷ ላይ በምታደርገው ቅዱስ ልብስ አኹን ቅሉ ሊረጋገጥ የሚችል እውነታ ነው፤ ለማጠቃለል ያኽል በመንገዶቿ ኹሉ በመለኮታዊ ጸጋ የተመላች ነበረች) በማለት የመልኳን አስደናቂ ደም ግባትና የአኗኗሯን ነገር መንፈስ ቅዱስ በገለጸለት መጠን ጥንታውያን አባቶች እነያዕቆብ የተናገሩትን መነሻ በማድረግ ጽፎታል፡፡

የአንጾኪያው ሊቀ ጳጳስ ዲሜጥሮስ በክርስቶስ ልደት በታኅሣሥ ፳፱ ዕለት በሚነበበው ድርሳኑ ላይ የእመቤታችንን የቤተ መቅደስ ሕይወት ሲያስተምር “At the moment when her mother Anna set her upon her feet, inside the door of the temple…” (እናቷ ሐና በካህናቷ ፊት በቤተ መቅደሱ በር ላይ ርሷን በእግሯ ባኖረቻት ጊዜ በራሷ ለጌታ መሥዋዕት ወደሚቀርብበት ወደ መሠዊያዉ መጋረጃ ወደ ቤተ መቅደስ እስክትደርስ ድረስ ኼደች፤ ከገባችም በኋላ ለመውጣት አልተመለሰችም በልቡናዋም የቤተሰቦቿ ሐሳብና ምድራዊ ነገራትን ከቶ አላሰበችም…እናም ባደገችና ስምንትና ዐሥር ዓመት በመላትም ጊዜ ለካህናቱ ኹሉ አብነት (ምሳሌ) ነበረች ርሷንም ለማየት ይፈሩ ነበር፤ መላ ሰውነቷ ንጹሕ ነበር ልቡናዋም በጌታ የጸና ነው፤በሥጋዋም በነፍሷም ንጽሕት ናት፤ ፊቷንም ከቤተ መቅደሱ በር ውጪ በፍጹም አላዞረችም፤ እንግዳ ሰውንም ከቶ አላየችም የወጣት ሰው ፊትን ለመመልከት ፊቷን ከቶ አላዞረችም፤ በቅድስና እግዚአብሔርን በማገልገል ለቤተ መቅደስ በመላላክ ኖረች እንጂ፤ ልብሷ ያማረ

እጥፋቱ በማኅተሟ ላይ ወደ ታች የወረደ ሲኾን የራሷ መሸፈኛም እስከ ዐይኖቿ ይደርሳል…በዐይኖቿ ላይ በጭራሽ መዋቢያ ቀለም አልተጠቀመችም፤ በጉንጮቿ ላይ ምንም ዐይነት የማጌጫ አበባ አላኖረችም፤ በእግሮቿ ላይ መጫሚያ ሰንደሎች አላደገረችም፤ በክንዶቿና በእጆቿ ላይ አልቦ ወይም አምባር ወይም ጌጣጌጥ አላደረገችም ነበር፤ ከልክ ያለፈ ምግብ በጭራሽ ፈልጋ አታውቅም፤ በከተማዋ የገበያ ስፍራ ውስጥ በጭራሽ ተገኝ አታውቅም፤ ለዚኽ ዓለም ሥራዎች በጭራሽ ጉጉት ዐድሮባት አያውቅም፤ ራሷን በጭራሽ ለመራቄት አጋልጣ እንዲኹም የአካላቷን ክፍሎች በጭራሽ በጥንቃቄ በአትኩሮት መርምራ አታውቅም) በማለት በቤተ መቅደስ በፍጹም ንጽሕናና ቅድስና መኖሯን መስክሯል::

እስክንድርያዊዉ ቅዱስ ቄርሎስም ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ከማብሠሩ በፊት የነበራትን የትሕትና ሕይወት ለተሰበሰቡት ሴቶች ሲያስተምር “Come, O all ye women who desire virginity…” (ድንግልናን የምትፈልጉ ሴቶች በሙሉ የጌታችን እናት የኾነችውን የማርያምን ምሳሌ ተከተሉ፤ የርሷንም መንገድ መናኛ ምግብ መብላቷንና መሬት ላይ መተኛቷን አስቡ፤ ለዚኽ ዓለም ነገሮች ምንም ዐይነት ጉጉት የላትምና የርሷ ስምም ኹልጊዜም በካህናት አፍ ውስጥ ነበር፤ ሰውነቷን በጭራሽ በሕዝብ መታጠቢያ ውስጥ ታጥባ አታውቅም፤ ራሷን በፍጹም በመዋቢያ የፊት ቀለም፣ በዐይን ኩልና በቅባት በጭራሽ አስውባ አታውቅም፤ በጣም ያጌጠ ልብስ እንደሚወድዱ ኹሉም በዘመኗ የነበሩ ሴቶች በደማቅ ባለቀለም ልብስ በጭራሽ አስጌጣ አታውቅም፤ በጭራሽ የወይንን ጣዕም ቀምሳ አታውቅም፤ ኹልጊዜም ዓለማትን የፈጠረ ፈጣሪዋን ትጠብቅ ስለነበር ፊቷን ወደ ምሥራቅ አዙራ ትቀመጥ ነበር፤ ከእናቷና ከአባቷ በስተቀር ከማንም ጋር ተገናኝታና አውርታ አታውቅም) በማለት የደናግል መመኪያቸው የኾነች የእመቤታችን የቤተ መቅደስ ሕይወት ለንጹሓን ደናግል አስተማሪ እንደነበር በስፋት ገልጾታል፡፡

የኢየሩሳሌሙ ቅዱስ ቄርሎስ በድርሳኑ ላይ የእመቤታችንን የቤተ መቅደስ ሕይወት ሲያስተምር “They (i.e Joachim and Anna) were in the habit of visiting their daughter once each month,…’’ (እነርሱ (ኢያቄምና ሐና) በወር አንድ ጊዜ ልጃቸውን በወር አንድ ጊዜ የመጐብኘት ልምድ ነበራቸው፤ ለርሷ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ይዘው ይመጡ ነበር፤ እናም ትንሿ ድንግል ልጃቸው ከርሷ በዕድሜ ከፍ ከሚሉ ደናግል ጋር በቤተ መቅደስ ታገለግል ነበር፤ እነርሱም በእጆቿ እንዴት መሥራት እንደምትችል ያስተምሯት ነበር፤ ርሷም ዐዋቂ በኾነች ጊዜ በራሷ ወደ ቤተ መቅደሱ ዐደባባይ ስትኼድ ከካህናትና ከአባቷ በቀር ማንም ወንድ ከቶ አይቷት አያውቅም…ትንሿ ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ ነበረች፤ የመላእክት አለቃው ገብርኤል በጣፋጭ መዐዛው ወደ ርሷ ቀረባት…የርሷ ውበቷ ምንም ወሰን አልነበረውም፤ ቤተ መቅደሱም ከጣፋጭ

መዐዛዋ የተነሣ በመላእክት ይመላ ነበር፤ ለንግግሯ ሲሉ ብቻ ይጐበኟት ነበረ) በማለት የቤተ መቅደስ አኗኗሯን በጥልቀት ገልጾታል። የወርቃማው ዘመን ሊቃውንት ከሚባሉት ውስጥ ተጠቃሹ ቅዱስ አትናቴዎስ "መልእክት (ደብዳቤ) ለደናግል" (Letter to Virgins) በሚል ሥራው ላይ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የቤተ መቅደስ ሕይወቷ ለደናግል ኹሉ አርአያና ምሳሌ እንደነበር ሲገልጸው "Mary was pure virgin, with a harmonius disposition..." (ማርያም ንጽሕት ድንግል ስትኾን በጣም ጥሩ አቋም የነበራትና መልካም ሥራዎችን የምትወድ ነበረች፤ በወንዶች መታየትን ፈጽማ አትፈልግም ነበር፤ ግን እግዚአብሔርን እንዲመረምራት ጠይቃዋለች፤ ያለማቋረጥ በቤቱ ውስጥ ቆይታለች፤ ከጨዋታ የራቀ ሰውን ኑሮ ትኖር የነበረ ሲኾን ማር ከምትሰጥ ንብ ጋር ትመሳሰላለች፤ በእጆቿ ከሠራቻቸው ሥራዎች የምታገኘውን ገንዘብ ለድኾች ታከፋፍላለች፤ በብቸኝነት ኹለት ነገራትን እንዲያደርግላት ወደ እግዚአብሔር ትጸልያለች፤ ይኸውም መጥፎ ሐሳብ በልቧ ውስጥ እንዳይሠርፅና ልቧ በጭራሽ ከፍቅር አምላካዊ እየቀዘቀዘ እንዳይኼድ ነበረ፤ ንግግሯ የተረጋጋ እና ድምፆቿም ዝግ ያሉ ናቸው፤ በየቀኑም መንፈሳዊ ርምጃ (ብቃታዊ መሻሻል ዕድገት) ማድረግ ትፈልጋለች፤ በየቀኑም ያነን ታደርጋለች፤ በጠዋት ስትነሣም ከዚኽ በፊት አስቀድማ ከሠራቻቸው አስበልጣ ሥራዎቿን ለመሥራት ትፈልጋለች፤ ሞትን ፈጽማ አትፈራም ነበር ይልቁኑ በሐዘን ኹና የመንግሥተ ሰማያት መዠመሪያ (መግቢያ) እንዳላቋረጠች በየቀኑ እያየች በጸሎቷ ታነሣለች) በማለት የደናግል መመኪያነቷን በስፋት ገልጾታል። ነቢዩ ዳዊት በመዝ ፺፩፥፲፪-፲፫ ላይ "ጻድቅ እንደ ዘንባባ ያፈራል፥ እንደ ሊባኖስ ዝግባም ያድጋል በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተተክለዋል፥ በአምላካችንም አደባባይ ውስጥ ይበቅላሉ" በማለት ቅዱሳን በእግዚአብሔር ቤት እንደሚኖሩ በምስጋናው እንደገለጸ ኹሉ የቅዱሳን ቅድስት እመቤታችንም በቤተ መቅደስ በንጽሕና በቅድስና ኖራለች።